**<u>የለውጥ ፐ/ፐ/ጥ/ት/የሥራ ሂደት (የፕሮጀክት ዕቅድ ክትትልና ግምገማ)</u>**

1.1. ዓላማ

ጎታች ነባርና ውጤት አልባ የሆኑ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በአዳዲስ አሰራሮች ለመተካትና ለማስተግበር የተለወጡ ወይንም የማስፈፀም አቅማቸው የተገነባ ተቋማትን መፍጠር

1.2. የስራ ሂደቱ ዋና ዋና ተግበራት

1. ግብዓት መስጠት
2. የትግበራ ዕቅድ መከታተያ ቼክ ሊሰት ዝግጅት
3. ክትትል፣ ድጋፍና የአፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ዋና ዋና ተግባራቱ ናቸው፡፡

1.3. ለስራ ሂደቱ የሚያስፈልግ የሰው ሀይል

- ለሥራ ሂደቱ 1 አስተባባሪና 2 ፈፃሚዎች በጠቅላላው ሶስት ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ

<u>የለውጥ ፐ/ፐ/ጥ/ት/የሥራ ሂደት በ2001 ዓ.ም የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

1. በአንደኛው ዙር የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ትግበራ በየደረጃው ያሉ 7 ሰክተር መ/ቤቶች አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ተመቻችቶላቸው ወደ ትግበራ ገብተዋል፡፡
2. በደንብ ቁጥር 72/2001፣ በአፈፃፀም ማኑዋሎችና ስትራቴጂዎች ላይ ለ 712 ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
3. በ1ኛው ዙር BPR ምደባ ያገኙት ሰራተኞች 648 ሲሆኑ መስፈርቱን ባለማሟላታቸው ምደባ ሳያገኙ የቀሩት 107 ናቸው፡፡
4. የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በዞን ደረጃ BPRን ለተገበሩ ለዞን መ/ቤቶች የውስጥ ቁሳቁስና የሰው ሀይል እንዲያሟሉ ብር 647.347 የገንዘብ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን በዚሁ በተፈለገው የገንዘብ ድጋፍ ሰክተሮች የውስጥ ቁሳቁስና ያለውን የሰው ሀይል እጥረት ለመቅረፍ ጥረት አድርገዋል፡፡
5. ክትትልና ድጋፍን በተመለከተ የለውጥ ፐ/ፐ የሥራ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ቼክ ሊስቶችን በማዘጋጀት ለ2 ዙር በዞንና ወረዳ ሰክተር መ/ቤቶች የመስክ ምልከታ በማድረግ

- BPRን የተገበሩ 39 ሰክተሮች ድጋፋዊ ክትትል በማካሄድ
- ለ140 የዞንና የወረዳ አስተባባሪዎች በትግበራ ግብረ መልስ ላይ ውይይት በማድረግ
- ከ 39 የወረዳ ሀላፊዎች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ በBPR መሬት እንዲተከል ተደርጓል፡፡

6. በገጠር ወረዳና ቀበሌ መልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈፃፀምን በተመለከተ ህብረተሰቡን በግልፅና በጋራ ስራ ለማሳተፍ አምኖ የመስራት ባህል ለማዳበር በየቀበሌው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ሞዴል ቀበሌዎችን፣ አርሷደሮችን ለመለየት በተደረገው ጥረት ስድስት ሞዴል ቀበሌዎች፣ አስር ሞዴል አርሷደሮችን በመምረጥ የእነዚህን ተሞክሮ በመጠቀም ሌሎች የተሸለ ስራ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡
7. በዞኑ ውስጥ ባሉ 56 ቀበሌዎች የቀበሌ ስራ አስኪያጆችና ተቆጥረው በወረዳ አቅ/ግ/ ባለሙያዎች ድጋፉ እየተደረገላቸው የራሳቸውን እቅድ አዘጋጅተው ወደ ትግበራ ገብተዋል፡፡
8. በፍ/ሥ/ማሻሻያ ፕሮግራም ፍ/ቤቶች ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት እንደክሱ ቅለትና ክብደት በአጭር ጉዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት መቻላቸው የጉዳዮች ክምችት ባለባቸው ወረዳዎች ተዘዋዋሪ ችሎትን በመሰየም አገልግሎት መስጠታቸው በየቀበሌው ማ/ፍ/ቤቶች ተደራጅተው እየተሰሩ በአከባቢው ፍትህን ማግኘት መቻሉ የሚጠቀሱ ዋና ተግባራት ናቸው፡፡
9. በአቃቤ ሕግ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች
    - አቃቤ ህጎችና ፖሊሲዎች በቅንጅት ሊሰሩ መቻላቸው
    - የቀጠር መራዘምን ለማስቀረት የተከሳሽና የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በአንድ ቀን እንዲሰጡ ማድረጉ
    - የፋይሎችን አያያዝ ዘመናዊ ለማድረግ ጥረት ማድረግ
    - የሕግ ንቃተ ትምህርት ለ13892 የህብረተሰብ ክፍል መስጠቱ
    - የምስክሮችን ወጪ መሸፈን ብር 33000 ተበርክቶ ይኸው ተግባራዊ መደረጉ የዘርፉ የአመቱ ጉልህ ክንውኖች ናቸው፡፡

10. የፖሊስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ክንውን በተመለከተ

- በገጠር በ56 ቀበሌዎች በከተማ በ6 በጠቅላላው በ62 ቀበሌዎች 22 ክላስተሮችን በማደረራጀትና የፀጥታ ኮሚቴ በማዋቀር በየአከባቢው የወንጀልን የመከላከል ሥራ ተሰርቷል የእርምት እርምጃም ተወስዷል፡፡

11. በ 62 የገጠር የወረዳ ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ በማቋቋም ህብረተሰቡ በወንጀል መከላከል የስራ ተሳታፊ እንዲሆን ተገርጓል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ለ76,165 የህረተሰቡ ክፍሎች ለኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

የማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር ጥረት እየተደረገ ሲሆን

በዚህ መሠረት

- በመኘታ ክፍላቸው የቴሌቪዥን አገልግሎት ማግኘታቸው
- ንፁህ ውሃ እንዲጠቀሙ መደረጉ ወንዶችና ሴቶች በተለያየ መኖሪያ ውስጥ መሆናቸው
- የወጪ ግዥና አቅርቦት በግልፅ ማስታወቂያ ማየት
- ከታራሚዎች ጋር የተቀናጀ ኮሚቴ በማዋቀር ግዥ እንደሚፈፀም
- መሠረተ ትምህርት እና በልዩ ልዩ የዕደ ጥበብ ሙያዎችና የጓሮ አተክልቶችን በማምረት የእስራት ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ ጥሩ ዜጋ ሆነው ተቀርፀው እንዲወጡ መደረጉ ዋና ዋና ክንውኖች ናቸው፡፡